የሰ/መ/ቁ. 49041

ኀዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሻገረ ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነ/ፈጅ ማህሌት ዳዊት ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ. አቶ ኤሣው መዓዛ

2ኛ. አቶ ዘርሁን ሙላት

3ኛ. ወ/ሮ ተስፋነሽ ተሰማ

} ጠ/መስፍን ደምሴ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዋስትና ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በአመልካች በኩል ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሁኖ ለ7 ዓመታት ያህል ትምህርት እንዲከታተል እና ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ለ6 ዓመት ያህል ለማገልገል ግዴታ ገብቶ ለ5 ዓመታት ያሕል ትምህርቱን ከተከታተለ በኂላ ባልታወቀ ምክንያት ትምህርቱንና ሥራውን ስላቋረጠ ለትምህርት የወጣውን ወጪ እንዲተካ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (ተጠሪዎችም) ለዚሁ ውል አፈፃፀም እስከ ብር 50,000 ድረስ የዋስትና ግዴታ የገቡ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ብር 29,497.03 ባልተነጣጠለ ሃላፊነት እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የመረመረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ(ተጠሪ) ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ሲወስን፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት አስቀድመው አስቀርተዋል በሚል ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካራከረ በኂላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በፍርድ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሰጡት ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1925/2/ መሰረት ከዋስትና ግዴታቸው ነፃ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በይዘቱም ተጠሪዎች የገቡት ግዴታ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ ለሚታሰብ ሁኔታ ስለመሆኑ ጠቅሶ ይህ ሃላፊነት ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታቸውን ማውረዳቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሚሸፈን ስለመሆኑ በመግለጽ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚያሳየው ነጥብ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ አውርደዋል ተብሎ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 125/2/ ተጠቅሶ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር ላይ እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እስፖንሰርንት ከፍተኛ ትምህርት ተከታትሎ አጠናቆ ሲመለስ ለ6 ዓመት ለማገልገል፣ ይህንን ካልፈፀመ ደግሞ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ያወጣውን የትምህርት ወጪዎች ሊተካ የውል ግዴታ የገባ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም 1ኛ ተጠሪ በውል የገባውን ግዴታ ካልፈፀመ እስከ ብር ሃምሣ ሺህ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለመክፈል የዋስትና ግዴታ መፈረማቸውም አላከራከረም፡፡

በዚሁ አግባብ አመልካች ይህንኑ ውለታ መነሻ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ እንደውሉ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ብር 29,497.03 እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቁ የሥር ፍ/ቤትም 1ኛ ተጠሪን ሃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ ውል የገቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋስትና ግዴታቸውን አስቀድመው አውርደዋል በሚል ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው ምርኩዝ ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ ወደፊት ስለሚሆን ወይም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ስለሚመጣ ግዴታ ዋስ ስለመሆን አስመልክቶ የዋስትና ግዴታው ለስንት ጊዜ እንደሚረጋ በስምምነቱ ያልተመለከተ እንደሆነ የዋናው እዳ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት ዋሱ ዋስትናውን ሊያስቀር እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው ዋናው ግዴታ ወደፊት ሊደርስ ወይም ላይደርስ በሚችል ሁኔታ ላይ (uncertain event) የተመሰረተ በሆነ ጊዜ ዋሱ ዋናው ግዴታ ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታውን ማስቀረት የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ዋናው ግዴታ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ግዴታ 1ኛ ተጠሪ ከሥራ ውጪ ሆኖ ትምህርት እንዲከታተል መፍቀድ እና ለትምህርቱም አስፈላጊውን ወጪ መሸፈን ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ትምህርቱን ተከታትሎ እንዳጠናቀቀ በውሉ ለተመለከተው ጊዜ ያሕል ለአመልካች አግልግሎት መስጠት አሊያም ለትምህርት የወጣውን ወጪ መተካት ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የዋናው ውል ግዴታ ወደፊት በሚደርስ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ እርግጠኛ ያልሆነ (uncertain event) ሁኔታ ላይ የተንጠለጠለ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1925 ሥር የሚሸፈን አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ዋና ግዴታ ወደፊት ሊደረስ ወይም ላይደርስ የሚችል ሁኔታ (conditional) ነው የማይሰኝ ነው ከተባለ ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋናው ግዴታ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት አስቀርተዋል ተብሎ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች 2ኛ ና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ የ1ኛ ተጠሪ ግዴታ ከመድረሱ በፊት ቀሪ ሆኗል በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አላፊነት የለባቸውም ሲል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ በመጥቀስ የሰጠው ፍርድ የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበና የግራ ቀኙን የውል ግዴታ በውል ያላመነ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 110168 በ01/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70425 በ16/10/2000 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤት በዚሁ መሰረት ያስፈጽም፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ